## ዳግማዊ ይሁዳ--የእምዬ ዕዳ

ከድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ

በጫና በፍርሀት
ፓርላማ ያላችሁ
ባለሥልጣን ሁላ
ጥቅም ያሠራችሁ
ሆድ አደር ሹማምንት
ከርስ ያታለላችሁ
ናላ በሆድ መሸጥ
ልምድ ያካበታችሁ
ሃገር ሲቸበቸብ
ዝምታ የገዛችሁ
መብላትም በሃገር
ማስተዋል ያጣችሁ
ወኔ በሆድ ሲያምጽ
የት ትገባላችሁ?
ፍርሃት ቤተኞችስ
የት ትከትማላችሁ?

ፖለቲካም ይሁን
ሥልጣኑንም ይውረስ
ሙስናውም መቼስ
ገንዘቡም ይታፈስ
በአንጃ ግራንጃ
ሕዝቡም ይተራመስ
ኑሮውም ሕይወቱ
ይቀጥል ይቃወስ
ስንኖር ደርበን
መከራን እንደልብስ
ሰማነው ሰሞኑን
የሚስጥሩን ድግስ
የሃገር ሽያጭ ሜራ
ክፉ ዕኩይ መንፈስ
አንፃራዊ ክህደት
ይሁዳ በኢየሱስ
ዳግም ተከሰተ
ባገሬ ዲያብሎስ

የክህደት ምሳሌን
ይሁዳ የምናውቀው
መምህሩን ጌታውን
ሸምቆ ሲሸጠው
ከሲኦል እንጦርጦስ
ፈጣሪ ዘፈቀው
ዘላለማዊ ሞት
ፍርድ አከናነበው

ሲኦልን ለመብለጥ
ምኞትም ሆነና
ያገራችን ርኩስ
ይሁዳን ሊያስቀና
የሲኦል ምቀኛ
ስለት ተሳለና
ድርድር ጀመረ
ህዝቡን ደበቀና
ደላላም ሳይፈልግ
ብቻውን ሆነና
እናቱን ሊሸጣት
አውጫጭኝ ወጣና
በሰሜን ጉድ ሲባል
ምዕራብ እንደገና

እናትም ላትሸጥ
ሃራም ሥጋ የሰው
ዳግማዊ ይሁዳን
ላይፈጥር ላይሳነው
ዘመቻን አወጀ
በአግባቡ ሊዳኘው
የሲኦል እንጦርጦስ
ፈጣሪያችን ሲያንሰው
የአዲስ ሲኦል መንደር
ግንባታውን ያዘው
አሮጌው ለዕኩዩ
ቀልሎ ስላገኘው

እናንተስ አልቅሱ
እኔስ አቁሜአለሁ
እንባዬ አልቆብኝ
ደሜን ጀምሬአለሁ
በሥጋ በደሜ
ይሁዳን ረግማለሁ
ፈጣሪ ይታረቀኝ
ሞትን እመኛለሁ
ዳግማዊ ይሁዳ
ይጠራ እላለሁ
ስለእምዬ ዕዳ
እኔ እማፀናለሁ
ቀን ዘላለም ሆኗል
ውሰደው እሬሣለሁ
አዲሲቷን ሲኦል
ለርሱ ናፍቄአለሁ

በክልልም በጎጥ
ዘራፍ የምትሉ
ቅንጅትም ህብረት
ተቃዋሚ ሁሉ
ኢ.ዴዩ ኢ.ህአፓ
አኩራፊ በሙሉ
ተቀናቃኝ ግንባር
እንቶኔ ሳትሉ
መናቆሩ ይቆይ
ድንበሯን ከልሉ
ለእምዬ በጡቷ
ይብቃ ተማማሉ
የህልውናን ፀር
ተባብራችሁ ጣሉ
መብላትም መናቆር
ባገር ነው እንዲሉ

***** * ***** * ***** * *****

© ድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ
ሰኔ ፳፻
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
June 2008